# የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት በአርሲ ዞን ማሳያነት[1]

ፍሬህይወት ባዩ[2]

**አኅጽሮተ ጽሑፍ**

የዚህ ጥናት ትኩረት የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት ጠቃሚ መሆኑን በጡት መጣባት እና በባህላዊ ዝምድና ማሳያነት የቀረበበት ነው። የጥናቱ ዋና አላማ፣ በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት መካከል በሰላማዊ አብሮነት ለመኖር ያስቻሏቸው በመጥፋት አደጋ ላይ የሚገኙ የመቻቻል መገለጫ ፎክሎሮችን ማስተዋወቅ ነው። ኢትዮጵያ በብሔረሰቦቹዋ ውስጥና መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ምን እንደሚመስሉ ተጠንተው አልተገለፁም፡፡ አይታወቁም፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሆነው በአርሲ ዞን፣ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የመቻቻል ማሳያ እሴቶች የፎክሎርን የጥናት መስክ ተከትሎ ማሳየት ነው። በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በሰላም ተከባብሮ ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል እሴቶች በተለይ በመጥፋት አደጋ ላይ የሚገኙት ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነት ጥናቱ ያተኮረባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው። ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነት በጥናቱ ክልል በተለይም በእስልምናና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል 'መቻቻል' የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ፣ መርህና ተግብራዊ ድርጊቶች ማለትም፡- አንዱ የሌላውን ኀልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣ መከባባርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንና ሰላምን፣ ወዘተ፣ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ምናልባትም በዓለማችን ልዩ ባህርይ ያለው የመቻቻል እሴት ፈጥረው ለዘመናት መኖራቸውን የተለያዩ ምሁራን አጽንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ Abdullah(2012)፣ Abbink(1998)፣ Braukamper(1992)። ብዝኀ-ባህል ከሚገለፅባቸው ቅርፆች መካከል አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች በተጓዳኝ መኖራቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያ በብሔረሰቦቹዋ ውስጥና መካከል በታሪክ የተገነባው የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ምን እንደሚመስሉ ተጠንተው አልተገለፁም፡፡ አይታወቁም፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በሆነው በአርሲ ዞን፣ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል የመቻቻል እሴትን ከሚያሳዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች መካከል ጡት መጣባት፣ እና ባህላዊ እምነትን ከፎክሎር ዕይታ አንፃር ማስተዋወቅ ነው። የብዝኀ-ባህል የግንኙነት መስተጋብር ባሕርያት ከሚገለፁባቸው እሴቶች መካከል አንዱ

[1] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ችግር ፈቺ ጥናቶች እንዲካሄዱ ለማበረታታት እ.ኤ.አ 2017 ዓ.ም ባወጣው የትልመ ጥናት ውድድር "Promoting Religious Tolerance for Peaceful Co-existance: The Case of Arsi" በሚል ርእስ ካለፉ ትልመ ጥናቶች አንዱ ነው።

[2] አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የስነጽሁፍና ፎክሎር ተመራማሪ፡፡

“መቻቻል” ነው። በተለይ የሃይማኖት መቻቻል ፅንሰ-ሀሳብ በየእለቱ በሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች አማካይነት ልዩነትን አክብሮ አንድነት እንዴት ጎልቶ እንደሚወጣ ማሳያ የሆኑ ባህላዊ ክዋኔዎችን በመጠቀም በተለያየ መስክ ለሚያጠኑ አጥኚዎች መነሻ ጥናት ማካሄድ ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡ የጥናቱ አላማ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና በእስልምና ሃይማኖት መካከል በሰላም አብሮ ለመኖር ካስቻሏቸው የመቻቻል መገለጫ ፎክሎሮች መካከል ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነትን ማስተዋወቅ ይሆናል። በዚህ ጥናት የተመለሱ የምርምር ጥያቄዎች፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በሰላም ተከባብሮ ለመኖር ያስቻሏቸው የመቻቻል ፎክሎር መካከል ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነት ሚናቸው ምንድን ነው? ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነት አሁን እንደማንኛውም ባህላዊ ክዋኔ የክዋኔ ደረጃቸው ምን ላይ ነው? የሚሉ ናቸው።

የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች ያሏቸው የአንድ ሀገር ህዝቦች በልዩነቶች ምክንያት ወደ ግጭት እንዳይገቡ ለመከላከል መፍትሄ ሊሆኑ ከሚችሉ መንገዶች አንዱ የመቻቻል እሴቶችን በጥልቀት የመረዳትና የማስተዋወቅ ስራ መስራት ነው። ልዩነትን ሳይሆን አንድነትን የሚያጠናክሩ ባህላዊ እሴቶችን ማስተዋወቅ የተለያየ ሃይማኖትና ብሄረሰቦች ላሏት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገሮች ሰላምን ለማስፈን በጋራ ሀገራዊ ልማት ላይ አብሮ ለመስራት ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። ይህ ጥናት ተጠኚው ህዝብ የፈጠራቸው፣ ያዳበራቸው እንዲሁም እየደበዘዙ ያሉ በሰላም ተከባብሮ የኖረበትን የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ ከሆኑ ባህላዊ እሴቶች መካከል ባህላዊ የዝምድና መፍጠሪያ ስልት የሆነውን ጡት መጣባትና መቻቻል የሚገለጽበትን ባህላዊ እምነት ለሌላው ለማስተዋወቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

የጥናቱ ወሰን፣ መቻቻል ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ በመሆኑ ከዚህ ውስጥ በሃይማኖት ልዩነት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ ያተኩራል። ከተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ብቻ ያተኩራል። መቻቻልን የሚያሳዩ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ቢኖሩም የዚህ ጥናት ትኩረት በመጥፋት ላይ ከሚገኙት ባህላዊ ዝምድና መፍጠሪያ ዘዴን እና ባህላዊ እምነትን ብቻ ይመለከታል።

## 2. የጽንሰ ሀሳብ መነሻ እና የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ክፍል የጥናቱን መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ የሚመለከት ብያኔ እና ጥናቱ ግብአት ያደረጋቸውን መረጃዎች ከየት በምን መንገድ እንዳገኛቸው የቀረበበት ነው። መቻቻል የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከተሰጠው የተለያዩ ብያኔዎች መካከል ለዚህ ጥናት የተሻለ የተባለውን ብቻ በመምረጥ በአጭሩ የተገለጸበት ክፍል ነው። በቅድሚያ የጽንሰ ሀሳብ መነሻ የሆነውን “መቻቻል”ን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 2.1 መቻቻል (Tolerance)

እንደ ዩኒስኮ የመቻቻል ብያኔ “መቻቻል የሞራል ግዴታ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ህጋዊ ቅድመ ሁኔታም ጭምር ነው። ለሠላም መስፈን አስፈላጊ ምግባር የሆነው መቻቻል የጦርነት ባህልን በሰላም እሴት ለመቀየር የራሱን አስተዋጽዎ ያደርጋል። መቻቻል፤ ሽንፈት፣ ውርደት ወይም

ጥቅምን አሳልፎ መስጠት አይደለም። መቻቻል ከሁሉ በላይ ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶችንና የሌሎችን መሠረታዊ ነጻነቶች እውቅና ከመስጠት የሚመነጭ አዎንታዊ አመለካከት ነው (UNESCO፣ 1995)።

መቻቻል በአንድ ሰው ፈቃደኝነት የተለያዩና ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን የመቀበል በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን እምነት ወይም አመለካከት ላይ እውነተኛ መሆን፣ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ፍርድ ከመስጠት መቆጠብ ማለት መሆኑን ያስረዳል። "መቻቻል" ሥነ-ምግባር ወይም ግብረ-ገብ ሲሆን የአንዱ ወገን እምነት "እውነት የሌለው ውሸት ወይም በተቃራኒው ነው ብሎ ትንተና ወይም ገለጻ ከመስጠት የተቆጠበ ነው" በማለት መቻቻልን ይገልጸዋል (Murphy 1997፡ 607-608)።

የመቻቻል ፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ከመልካም አተያይ ጋር የተቆራኘና በተግባር የሚገለጽ የማህበራዊ ግንኙነት መስተጋብር ነው። መቻቻል ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ቡድንና እስከ ሀገር እንዲሁም በመንግሥታት መካከል የሚገለፅ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። መቻቻልን በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ እንዲህ ነው ብሎ ለመተንተን ከመሻት ይልቅ በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ባለ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት አስተውሎት ላይ ተመስርቶ የሚጠና ነው፡፡

መቻቻል ከሚታይባቸው መካከል የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ ቡድኖች ሲሆኑ ይህም የሃይማኖት መቻቻል በሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚታይ ይሆናል። በሃይማኖት መቻቻል ብያኔ "የሌሎችን ሃይማኖት ከራሳችን ሃይማኖት ጋር በማንኛውም መለኪያ ብንመዝነው ወይም ብናነፃጽረው 'መጥፎ ነው!' የምንልበት መለኪያ የለንም"(Newman 1978፡ 179)። በማለት የእኔ ሃይማኖት ትክክል ነው የሌላው ልክ አይደለም የሚለውን መለኪያ ሳያነሱ የየራስን ሃይማኖት የያዙ ቡድኖች አንድ የሚሆኑበት የጋራ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው። ሃይማኖታዊ መቻቻል በአንድ አካባቢ በጉርብትና በሚኖሩ በተለያየ የሃይማኖቶች ተከታይ ግለሰቦች ወይም ማህበራዊ ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የመቻቻል አንዱ ገጽታ ሲሆን የፎክሎር አንዱ አብይ ዘርፍ በሆነው በሀገረ-ሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚጠና ነው። መቻቻል የምንለው ተቀራርበው ወይም አብረው በሚኖሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል በተግባር የሚገለጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው።

አብሮነት ሁለት የተለያዩ ቡድኖች አብረው ሲኖሩ ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት የሚፈጥሯቸው የጋራ ጉዳዮች ሲጎዳኙ ያለው ግንኙነት ሰላማዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው። የአብሮነት ጽንሰ ሀሳብ ከመቻቻል ጽንሰ ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው። መቻቻል የምንለው እና በሁለት ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚገለጽን አንዱ ለሌላው ያለውን አክብሮት በተለይም ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ጉዳይ አብሮ መሆንን የሚያሳይ ነው፡፡ ሰዎች አብሮ በመኖር ልምድ ተመክሮ ያገኛሉ። በተመክሯቸው ምን መሥራትና አለመሥራት እንዳለባቸው ምርጫ በማድረግ መልካም ወደ ሆነው ሁሉ ምን እንደሚመራቸውና እንደማይመራቸው ያውቃሉ። "አብሮነት" የተሻለ የኑሮ ግንኙነት ስልት ለመፍጠር ማህበራዊ መተሳሰብን ለማጠናከርና አካባቢን ምቹ ለማድረግ የሚያግዝ የመቻቻል ባሕርይ ነው(Jhon 2001፡ 64)። መቻቻል የግድ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው። በመሆኑም አብሮነት እነዚህ ቡድኖች በሰላም አብረው ለመኖር አንዱ የሌላውን እምነትና ድርጊት አክብሮ መገኘትንም ያስገነዝባል።


### 2.2 የጥናቱ ዘዴ

የመቻቻል ባሕርያትን ለመረዳትና ባህላዊና ማህበራዊ የመከሰቻ ገጽታዎችን ለመለየት በይበልጥ በአውድ ላይ የተመሠረቱ የአይነት (qualitative) ወይም የትርጉም (interpretative) መረጃዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡ ከተጠኚው ህዝብ እይታ አንፃር ወጥ ወይም አዲስ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል “ቀዳማይ” (Primary) የመረጃ ምንጭ አንዱ ነው። ሁለተኛው፣ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ሲሆን ከተለያዩ ጽሁፎች እና ተዛማጅ ምንጮች የሚገኝ ነው፡፡ በሁለቱም የመረጃ ምንጮች አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ ሂደት ውስጥ ከመስክ መረጃ ለማሰባሰብ ወደ ህዝቡ ሲገባ ‘ውስጣዊ እይታን’ (Emic, insider’s view) እና ‘ምሁራዊ እይታ’ (Etic, outer’s perspective) ሚዛናዊ ማድረግ ይጠበቅበታል (Fetterman 2009: 32)፡፡ በዚህ ጥናት ሁለቱን እይታዎች ሚዛናዊ በማድረግ ጥናቱ ተከናውኗል። ከመስክ መረጃ ሲሰበሰብ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። እነዚህም ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ናቸው።

### 3. አካባቢያዊ ዳራ

ለጥናቱ የተመረጠው ኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ነው። በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳና የበቆጂ ከተማ አስተዳደር ናቸው። የአርሲ አስተዳደራዊ መዋቅሩ በ24 የከተማ አስተዳደርና በ497 የገጠር ቀበሌዎች የተከፈለ ነው። አዋሳኞቹም በምስራቅ ሀረርጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ሸዋ፣ በደቡብ ባሌ ዞን፣ በምእራብ ደግሞ ምእራብ አርሲ ይገኛሉ። አርሲ ዞን በካርታ[3] የሚከተለውን ይመስላል።

[3] ካርታው ከዚህ ቀደም በአርሲ ዞን በ2009 ዓ.ም በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ለተደረገ ጥናት በባለሙያ የተዘጋጀ ነው።




ማእከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ ባደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት በአርሲ ዞን የሚኖረው ህዝብ 2,957,817 ይሆናል (CSA 2007-2008)። ከዚህ ውስጥ ወንዶች 1, 483,934 ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 1,473, 883 እንደሆኑ ያመለክታል። የከተማና የገጠር ነዋሪ ስብጥር የገጠሩ ነዋሪ 2, 591,066 ሲሆን የከተማ ነዋሪው ደግሞ 366,751 ነው። ከዚህ ውስጥ በሌሙና ቢልቢሎ የሚኖረው ህዝብ ብዛት 181,789 እንደሆነ ይገልጻል። ከነዚህ መካከል የገጠር ነዋሪ 158, 459 ሲሆን 23,330 የከተማ ነዋሪዎች ናቸው። የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር በ2002 ባደረገው ቆጠራ ደግሞ አጠቃላይ የህዝቡ ብዛት 204, 458 ሲሆን ወንዶች 105, 371፣ ሴቶች ደግሞ 10,381 ይሆናሉ (የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር 2002፡ 15)።

የወረዳው ነዋሪዎች በ1998 ዓም በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን (የኢ.ኦ.ተ.ቤ)፣ የእስልምናና የፕሮቴስታንት[4] ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በጥናቱ ከመስክ በተገኘ መረጃ ከቆጠራው በኋላ በአካባቢው የተዋወቁ በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ጥቅል ስም የሚጠሩ እና ከዚህ ውጭ የሆኑም እንዳሉ መረጃ ሰጪዎች እንዲሁም በምልከታ የተገኘው መረጃ ያሳያል። “በ2003 ዓ.ም ቃለ-ህይወት ቤ/ን ተመሰረተች። ህይወት ብርሀን ቤ/ን ደግሞ በ1997/1998 አካባቢ ተመሰረተች። የህዋርያት ቤ/ን ደግሞ

[4] ፕሮቴስታንት በሚባለው ትልቅ ጥላ ስር ተካተው የሚጠሩት፡- ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን፣ ጴንጤ ቆንጤ (Pentecostal)፣ መካነ እየሱስ (Luteran)፣ መጥምቃዊያን፣ አንጀሊካን (Anglican)፣ ፕሬስቢተሪያን ቤተክርስቲያን (Presbyterian)፣ መሰረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ህይወት፣ ወዘተ(እስታስቲክስ ኤጀንሲ፣ 2007፣ 71) በእዚህም ጽሁፍ ውስጥ ከዚህ በኋላ ፕሮቴስታንት በሚለው መጠሪያ የሚጠቀሱት እነዚህ ናቸው።

(የሀዋሪያት ቤ/ን ከስድስቱ ጋር ህብረት የላቸውም፤ የአምልኮ ስፍራቸውም ለብቻ ነው።) በ1990ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ተመሠረተ።[5]

በተለይ የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች የሚከተሉትን ሃይማኖት በተመለከተ "ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?" ተብለው ሲጠየቁ ሙስሊም ወይም ክርስቲያን ብለው ይመልሳሉ። ሆኖም ከዚሁ ጎን ለጎን ባህላዊ የሆኑ እምነቶችንም ይከተላሉ።

የወረዳው ነዋሪዎች የሃይማኖት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ህብረት ይፈጥራሉ። ማህበራዊ ግንኙነቱን ለመፍጠርም ሆነ የተመሠረተው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረውና መሠረት እንዲይዝ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች ሚናቸው ተመጣጣኝ ነው። ማህበራዊ መስተጋብሮቹ በኑሮ ውስጥ አንዱ ወደ ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች በመሄድ ይገናኛሉ። አጋጣሚዎቹም ባህላዊ መድሃኒት በመስጠትና በመቀበል፣ እድር አብሮ በመግባት፣ ባህላዊ የእምነት ስፍራዎች በጋራ የሚከወኑ ክዋኔዎች ላይ በመካፈል እንዲሁም የተጣላን በማስታረቅ የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።

### 4. የሃይማኖት መቻቻልን ማስተዋወቅ ለሰላማዊ አብሮነት

በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ለሰላማዊ አብሮነት አስተዋጽዖ ያላቸው የመቻቻል ባህላዊ እሴቶች በተለይ ጡት መጣባት እና ባህላዊ እምነትበማህበረሰቦች መካከል ልዩነትን ጠብቆ አንድነትን ለማጎልበት እና በሰላም አብሮ ለመኖር ያስቻሏቸውን ክዋኔዎች ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በዚህ ክፍል ቀርቡዋል። ማህበረሰቡ እነዚህን ባህላዊ የመቻቻል እሴቶች መገለጫ ካለፈው ትውልድ ተቀብሎ ዛሬ ይከውነዋል፣ በተግባር በማሳየት ያስተዋውቋቸዋል።

#### 4.1 "ጡት መጣባት"

ጡት መጣባት ሃይማኖታዊ ገደብ የሌለበት የሥጋ ዝምድና በሌላቸው ሁለት ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች መካከል በፈቃደኝነት የዝምድና ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ትውፊታዊ ደንብ ነው፡፡ ጡት ጠቢ የሚባለው ዝምድናውን ፈልጎ የጠየቀው ግለሰብ ሲሆን ተጠያቂው ወይም ተለማኙ ደግሞ ተጠቢ ይሆናል። ጡት ልጥባ ወይም ልዛመድ ብሎ የሚጠይቀው ዝምድናውን የሚፈልገው ወገን ሲሆን ለዚህም በባህላዊ ደንቡ መሠረት አስፈላጊ የሆነውን ክዋኔ መፈጸም ይኖርበታል። ዝምድናው ሲገለጽ ዘመድ ነን ለማለት "ጡት ነን ወይም ጡት ናቸው" ይባላል። እከሌ "የእኔ ጡት ነው" ከተባለ ዘመዴ ነው ማለት ሲሆን በስጋ ዝምድና ሳይሆን በባህላዊ መንገድ የተዛመዱ እንደሆኑ ይታወቃል። ይህንን ባህላዊ ልማድ የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ ያደረገው በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል መከወን መቻሉ ነው።

[5] መጋቢ ብሩክ አለሙ፣ እድሜ 46፣ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ፣ የሌሙና ቢልቢሎ ሙሉ ወንጌል ቁጥር አንድ ቤተ-ክርስትያን አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም የወረዳው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አስተዳዳሪ(ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 19/2009)፡፡

የጡት ልጅና የጡት አባት የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች በአማርኛ መዝገበ ቃላት የሚፈቱበት መንገድም ተመሳሳይ ነው። የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃል "ጡት ተጣባ" የሚለውን የጡት ልጅና የጡት አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመዱ "ጡት አጣባ" የሚለውን ደግሞ "የጡት ልጅ አደረገ" በማለት ይተረጉመዋል። እንዲሁም የጡት ልጅ ከትውልድ ሀረግ ውጭ የሆነና የአንድ ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሲሆን የጡት አባት ደግሞ አውራ ጣቱን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ግለሰብ ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ የአማርኛ መዝገበ ቃል ደግሞ ይህንኑ ሀሳብ ሰፋ በማድረግ እንደሚከተለው ብያኔ ሰጥቷል። "ጡት ተጣባ" የጡት ልጅና አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመዱ። "የጡት ልጅ" ማለት ደግሞ ከትውልድ ሃረግ ውጭ የሆነና የአንድ ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሰው ሲለው "የጡት አባት" የሚለውን ደግሞ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ) በማር የተነከረ ጣቱን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ሰው" (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962) በማለት ይበይነዋል።

በዚሁ የአማርኛ መዝገበ ቃል "የጡት እናት" የሚለውን ቃል ፍቺ በመስጠት ሴትም የጡት እናት እንደምትሆንና በዚህ ባህላዊ ልማድ ዝምድና እንደምትመሠርት ቢጠቁምም በዚህ ጥናት የተገኘው መረጃ ግን ጡት መጣባት በወንዶች መካከል የሚከወን ባህላዊ ልማድ እንጂ ሴቶች ወይም ሴትና ወንድ ይህንን ሥርዓት አይፈጽሙም።

ጡት መጣባት ከጉዲፈቻ ባህላዊ የዝምድና መንገድ ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም የተለየ ባህላዊ የዝምድና መንገድ ነው። በሃይማኖት የተለያዩ ሁለት ቤተሰቦች በጉዲፈቻ አማካይነት ዝምድና መፍጠር ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የተደረገ ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት አስተያየት የሚበረታታ አይደለም። የዚህ አንድምታም ዝምድናን ከማጥበቅ ይልቅ ልዩነቱን አለማክበርና ቅሬታን በእስልምና እና በክርስትና ሃይማኖት መካከል የሚፈጥር ያደርገዋል።

ዝምድናው የሚፈጸመው ለረጅም ጊዜ በሚተዋወቁ በሚግባቡና በሚዋደዱ ወገኖች መካከል ያለው ወዳጅነት ጠንካራና ዘላቂ መሠረት እንዲኖረው ነው። የመዛመዱ ምርጫም በሦስተኛ ወገን የሚወሰን ሳይሆን ዝምድናውን በፈለገው እና ዝምድናው በተፈለገው ግለሰብ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ጡት ጠቢውም ተጠቢውም (በሁለት ግለሰቦች) መካከል የሚመሠረት ዝምድና በቤተሰቦቻቸውና በቤተ-ዘመድ መካከል የጸና ይሆናል። በተለይ በጣም በሚቀራረቡ ቤተሰቦች መካከል የሚደረግ የጡት መጣባት ምክንያቱ የነበረው ወዳጅነት ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ ነው[6]።

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ የሚከናወነው የጡት መጣባት ባህል በአብዛኛው የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ግለሰቦች መካከል ወይም ከሁለቱ በአንዱ ሃይማኖት ተከታይ ግለሰቦች መካከል ይካሄዳል። በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ. ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ጋብቻ ስለማይፈቀድ ሁለት ወዳጅነት ያበጁ ቤተሰቦች የጋብቻ ያህል ለመዛመድ ጡት መጣባትን

[6] አለሙ ባጫ (ቃለ መጠይቅ መጋቢት 23 2009)።

ይመርጣሉ[7]። የዝምድና ሥርዓቱ ጋብቻ ለመፈጸም ከልመና ጀምሮ እስከ ጋብቻው ዕለት የተለያዩ ሂደቶች እንዳሉት ሁሉ ጡት መጣባትም እንደዚሁ በተመሳሳይ ሂደት ውስጥ ያልፋል።

የጡት መጣባት ሥራት-ክዋኔ የሚፈፀመው በጡት አባት ቤት ነው። በቀጠሮው ዕለት የጡት አጥቢው ድግስ ደግሶ፣ ዘመዶቹን በሙሉ ጠርቶ፣ ጡት ጠቢውን ይጠብቀዋል። በዚህ ሥነ-ሥረዓት ላይ የሚታደሙት ለዝምድና የተፈላለጉት ግለሰቦች የቅርብ ዘመዶች እንዲሁም ለዝምድናው መሳካት የደከሙ ሽማግሌዎች ናቸው። የጡት አባት የጡት ልጁን ከአብራኩ ከወጡ ልጆቹ፣ ከስጋ ዘመዶቹ ለይቶ ላያይ፣ ችግሩን እንደ ራሱ ችግር አድርጎ ሊወስድ፣ ልጁም እንደዚሁ የጡት አባቱን ልክ እንደ ወላጅ አባቱ፣ ዘመዶቹንም እንደ ሥጋ ዘመዶቹ አድርጎ የሀዘን የደስታ ተካፋይ እንዲሆን የሚያስገድድ ቃል ኪዳን የሚገቡበት ነው። በሥነ-ሥርዓቱም ላይ የተገኙት የጡት አባት ወገኖች የጡት ልጅ የሚሆነውን ግለሰብ እና ቤተሰቡን እንደ ሥጋ ዘመዳቸው ሊቆጥሩት ቃል ይገባሉ።

ዝምድናው ሲመሠረት በአብዛኛው የእድሜ ገደቡን ስናይ እራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ወጣቶች እና ጎልማሶች ዝምድናውን ይጠይቃሉ። አንድ ወጣት አባት እናቱ በህይወት ኖሩ አልኖሩ ዝምድናውን ለመመስረት አያግደውም። ሆኖም ወላጅ አባቱ በህይወት ካለ የጡት አባት የፈለገው ልጅ አባቱን ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር ዝምድናው ወደተፈለገው ግለሰብ ዘንድ ይልከዋል። አባትም ተመላልሶ ተጠያቂ እሺታውን እስከሚገልጽ ይጠብቃል። ተለማኙ አባት እሺታውን ከገለጸ በኋላ የዝምድናው ባህላዊ ክዋኔ የሚፈፀምበትን ቀን ቀጠሮ ይወስናሉ። የዝምድናው መመስረቻ እለት ቤተሰቡ በተለይ እናት አባት አያት ጡት የሚጠባውን ግለሰብ አጅቦ ወደ ጡት ተጠቢው ቤት ይሄዳሉ። ዝምድና ጠያቂው በዚህን እለት ባዶ እጁን አይሄድም። ለሚዛመደው ግለሰብ እንዲሁም ለሚስቱ ስጦታ የሚሆን ልብስ እና በእለቱ የሚበላ ምግብ ባበህሉ የተለመደውን ገንፎ ወይም በግ ይዞ ይሄዳል።

ሥርዓቱንም ለመፈጸም የጡት ተጠቢው ባለቤት እንዲሁም የተጠራው ዘመድ ባለበት ነው። የሚጠባው ዝምድናው የተፈለገው ግለሰብ ጡት ሲሆን ጠቢው ደግሞ ዝምድናውን የጠየቀው ግለሰብ ነው። ለዚህ ሥርዓት መፈጸሚያ ማር የግድ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ሥርዓቱን ሲገልጹ "የተጠቢውን ጡት የጠቢው እናት ማር ትቀባዋለች። ያን ማር የተቀባ ጡት ጠቢው ሶስት ጊዜ ይጠባዋል።"[8] ከዚያም የተቀመጡት ሽማግሌዎች ተጠቢው ከልጄ ላልለየው ብሎ ቃል እንዲገባ ያደርጉታል። እሱም ቃል ይገባል።

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ ያለው "ጡት" ተብሎ የሚጠባው እንዲሁም ማሩን የምትቀባው ከአንዱ አካባቢ፣ ሌላው አካባቢ ልዩነት አለው። ልዩነቱ ማሩን በሚቀባው ማንነት ነው። አንዱ አካባቢ ማሩን ቀቢዋ ልጅ ለመሆን የጠየቀው ግለሰብ እናት ነች። በሌላው አካባቢ ማሩን የሚቀባው ልጅ ለመሆን የጠየቀው እና ማሩን እንደጡት የሚጠባው ግለሰብ እራሱ ነው። የሚጠባው ደግሞ ጡት ሳይሆን የቀኝ አውራ ጣቱን ጡቱ ስር በማድረግ ልክ እንደጡት አውራ

[7] ጀማል ዋቤ(ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 6 2009)።

[8] ጀማል ዋቤ (ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 6 2009)።

ጣቱን ይጠባል። ይህንን ሥራት ክዋኔ ከፈጸሙት መካከል አንደኛው ሲገልጹ፤ "ጡት የምጠባው ሰውዬ አውራጣቱን ማር ውስጥ ነክሮ ጡቱ ስር አስጠጋው እኔም ያንን አውራ ጣቱን ጠባሁ፣ በዚህ መልኩ ሶስት ጊዜ ማሩን እየነከረ ይጠባል።"[9] ከዚያም አጥቢው ከስጋ ዘመዶቹ ላይለየው፣ በችግሩ ጊዜ ሊደርስ፣ ለዘመዶቹ የሚያደርገውን ሊያደርግለት ቃል ይገባል። በሥርዓቱም ላይ የተገኙት የተጠቢው ዘመዶች እንዲሁ እንደ ስጋ ዘመዳቸው ሊቆጥሩት ቃል ይገባሉ። ለምሳሌ፡- 'አንተ ጡት የምትጠባው ታላቅ ወንድማችንን ብቻ አይደለም። እኛ በሙሉ ጎሳዎቹ ነን። ያልመጡም ብዙ ዘመዶች አሉን፤ ስታገኘን ሰላም በለን። ስትቸገር መጀመሪያ ለአባትህ ንገር፣ ከእርሱ አቅም በላይ ከሆነ መጥተህ ለእኛ ንገረን። ጡት መጣባት ማለት ይሄ ነው። ...ዝምድናውን እግዚአብሄር ቀና ያድርገው ብለው ይመርቃሉ[10]። ይሄም ቃል እስከ ሰባት ቤት ድረስ ጋብቻ መጋባትን፣ እንዲሁም ከሌላው ዘመድ ጋር ጡት መጣባትን ይከለክላል።

የዝምድና ማጽኛው ቃል ኪዳን የመግባቱ ክዋኔ ከተፈጸመ በኋላ የሚቀርበው ማእድ ዝምድና ጠያቂው ያመጣው ይሆናል። የጡት መጣባት ሥርዓት ሲፈጸም የሚዛመዱት ወገኖች የሃይማኖት ልዩነት ካላቸው ክዋኔው ላይ የሚለየው በሚቀርበው ማእድ ብቻ ነው። የመጣው ገንፎ ከሆነ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም በአንድ ገበታ ይቀርባል፤ ይበላል፡፡ በአብዛኛው የጡት ልጅና የጡት አባት ወገኖች አንድ ሃይማኖት ተከታይ ቢሆኑም፣ ባይሆኑም፣ ገንፎ ሁሉንም በአንድ ማዕድ የሚያሰልፍ ምግብ ነው። እንግዶቹ በገንፎ ምትክ ያመጡት በግ ከሆነ የጡት አባት እንዲባርከው ይደረጋል። ዝምድናውን የፈጠሩት ወገኖች በሃይማኖት የተለያዩ ከሆነ የጡት አባት ሌላ በግ ይሰጣል። ስጋው እንዳይተርፍ በአካባቢው ያሉ ጎረቤቶች ይጠራሉ። ከዚህ ውጭ በባህላዊ ክዋኔው ላይ ልዩነት የለም።

ጡት የመጣባቱ ሥነሥርዓት የሚያበቃው ሁለቱ ቤተሰብ እንደገና ተገናኝቶ ሲቀላቀልና በደንብ እንዲተዋወቁ ከተደረገ በኋላ ነው። በሌላ ቀን ጡት የጠባው ሰው በቤቱ ድግስ ደግሶ ጡት ተጠቢውንና ዘመዶቹን ይጠራል። ለዚህ ድግስ ሲመጡም የጡት አባትና ቤተሰቡ ለጡት ልጁና ቤተሰቡ ስጦታ ይዘው ይሄዳሉ። ይሄም የሁለቱን ወገን መዛመድና መቀላቀል ያመለክታል። ከዚያ በኋላ ከሩቅ የስጋ ዘመዱ የበለጠ የክፉ ቀን ደራሽ ዘመዱ ይሆናል። ዝምድናውም ጡት የተጣባውን ዘመዶችና ጎሳዎች በሙሉ እንደስጋ ዘመዱ ይመለከታቸዋል፤ እነሱም እንደዚያው።

አንድ ሰው ከአንድ በላይ የጡት ልጆች ሊኖሩት ይችላል። ለዚህ ጥናት መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት ጡት የተጣቡ መረጃ አቀባዮች እንደሚገልጹትና እንደተገበሩት በሚያሳዩ መረጃዎች ውስጥ አንድ ሰው የተለያየ ጎሳ ያላቸውን ሰዎች ጡት ይጠባል። በዚህም መሠረት ትንሹ አንድ ሲሆን ሁለትና ሶስት በተደጋጋሚ የሚገጥም ሲሆን ትልቁ ስምንት ነው። "ስምንት ሰዎችን ጡት ጠብቻለሁ[11]።" ጡት የተጣቡትም ከእስልምና ሃይማኖት ተካተዮች ጋር ሲሆን ከተጣቡ በኋላ እስካሁን ለሰላሳ አምስት አመታት እንደስጋ ዘመድ እንደሚጠያየቁና በችግርም ጊዜ እንደሚረዳዱ

---

[9] ባዩ ተስፋዬ (ቃለ መጠይቅ ጥር 7/ 20009 ዓ.ም)
[10] አለሙ ዋሴ ( ሚያዝያ 6 2009)።
[11] አባ ገዳ አለሙ ባጫ (ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 4 2009)።

ይገልጻሉ። "ጡት ከተጣባን በኋላ በሃይማኖት ባንገናኝም የምንተያየው እንደ ስጋ ዘመድ ነው[12]።" ሌላውን መረጃ አቀባይ ስንመለከት "እኔ ስድስት ክርስቲያኖች ጋር ጡት ነን"[13] በማለት ይናገራሉ።

በደንቡ መሠረት የጡት መጣባት ዝምድና እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ጋብቻን ብቻ ሳይሆን በዚህ መልክ ዝምድና በፈጠሩት ወገኖች መካከል ጡት መጣባትም የተከለከለ ነው። አንድ ሰው የተለያየ ጎሳ ካላቸው ከአንድ በላይ የጡት ልጆች ወይም የጡት አባት ሊኖሩት ይችላል። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው የጡት ልጅ ዝምድናው እንደ ጋብቻ ሁሉ ዝምድናን ለማጠናከር በቦታ ቢራራቁም እንደዘመድ ለመጠያየቅ ሲሉ የሚተገብሩት መሆኑን ነው።

በጡት ልጅነት የሚገኘው ዝምድና በዋናነት ምክንያቱ ጡት ጠቢው ከጡት ተጠቢው ማግኘት የሚፈልገው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ስነልቦናዊ እና የመሳሰሉትን ጠቀሜታዎች ታሳቢ የደረገ ነው። በተለይም በአካባቢው ብዙ ዘመን የኖሩና በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ በተለያየ መልኩ ከበሬታን ያተረፉ ግለሰቦች የጡት አባት እንዲሆኑ ይጠየቃሉ። ምክንያቱም የጡት ልጁን በተለያየ መልክ ማጥቃት የፈለገ ወገን ያንን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን የጡት አባቱን እንደደፈረ ያስቆጥረዋል። በዚህ መልክ ከለላ የሚፈልጉ ወገኖች የጡት አባት ለምኖ እሺ ከተባለ ስርዓቱን ፈጽሞ ለማንኛውም ጉዳይ ከለላ የሚሆን ዘመድ በባህሉ ደንብ ያፈራል። ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የሚፈልጉ ደግሞ በአካባቢው የሀብት መለኪያ መሰረት ሀብታም ነው ያሉትን ግለሰብ የጡት አባትነት ፈቃድ ጠይቀው ይዛመዳሉ። የጡት አባትም ለማንኛውም ዘመዱ የሚያደርገውን እገዛ ያደርግለታል። የጡት ልጅነቱ መመስረቻ ምክንያቶች የተለያዩ ይሆኑና በሂደት ግን ሁለቱ ቤተሰብ ዝምድናውን አጠንክሮ ሲኖር ደጓሚው፣ ተደጓሚ ከለላ ፈላጊው፣ ከለላ የሆኑባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። በመስክ መረጃ ጡት ልጅ ያላቸውን ብዛት ስንመለከት ትልቁ ስምንት[14] ሲሆን ትንሹ አንድ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከአንድ በላይ የጡት ልጅ ሊኖረው ይችላል።

በአጠቃላይ ጡት መጣባት በሥጋ ዝምድና የመተሳሰርን ያህል ባዕዳን በሆኑ፣ በሃይማኖትም በተለያዩ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ማህበራዊ ክፍሎች መካከል አብሮነትን የሚያረጋግጥ መተሳሰብን የሚፈጥር የመቻቻል ገጽታ ነው፡፡ ጡት መጣባት በተቸገሩ ጊዜ ለመረዳዳት፣ በደስታ ጊዜ ደስታን አብሮ ለመጋራት፣ እንደ ልጅ ለመተያየት ያም የጡት ዘመድ ሲሞት ቤተሰቡን ልጆቹን ለመርዳት ነው። ጡት መጣባት ለሁሉም የህብረተሰቡ አባላት ተሳትፎ ክፍት ወይም የሚያበረታታ ባህላዊ የዝምድና መመስረቻ ስልት ነው። የጡት መጣባት ዝምድና በግለሰቦች ፍላጎት ላይ የተመሠረተና በራሳቸው ምርጫ የሚከናወን ሰብአዊ ግንኙነት መፍጠሪያ ስልት ነው። ልዩነትን በማክበር መተዋወቅ፣ መቀበል፣ መቀራረብ፣ እንደ ሥጋ ዘመድ መተሳሰር፣ መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ አብሮነት፣ ወዘተ፣ ሁሉ በመርህም በድርጊትም የሚያጠቃልል ልዩ የሆነ ባህላዊ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

[12] አባ ገዳ አለሙ ባጫ (ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 4 2009)።
[13] ጀማል ዋቤ (ቃለመጠቅ ሚዝያ 8 2009)።
[14] አቶ አለሙ ባጫ ፣ እድሜ 76 የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ (ቃለ መጠይቅ)። መረጃ አቀባይ ሲሆኑ በተግባር አራት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ አራት የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ የጡት ልጆች አሏቸው።

## 4.2. ፎክ (ትውፊታዊ) እምነት

'ፎክ-እምነት'፣ 'ትውፊታዊ (traditional) እምነት' ተብሎም ይጠቀሳል (Degh 1972)፡፡ 'ትልልቅ' ተብለው የሚጠቀሱትን፣ ለምሳሌ፡-የክርስትና፣ የአይሁድ፣ የእስልምና፣ የቡድሀ፣ ወዘተ፣ ሃይማኖቶች እምነቶችንም ጨምሮ የሚይዝ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ "የእምነት ሥርዓት የፎክሎር ጥናት ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳብ ነው (Motz 1998:340)። እንደ አንድ የፎክሎር ዓይነት (genre) እምነት … ርዕይዮተ-ዓለምን፣ ሥነ-ኅላዌን (cosmological)፣ የሰማያውይውንና የምድራዊውን አፈጣጠር፣ መንፈሳዊ እምነቶችን፣ ወዘተ፣ ሁሉ የሚያካትት ሰፊ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። ጠበብ አድርገን እንውሰድ ብንል እንኩዋን መናፍስትን፣ መተትን፣ ድግምትን፣ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ሥርዓተ-በዐላትን፣ ገድሎችን፣ ተአምራትን፣ ሙዋርትን፣ ባህላዊ ህክምናን፣ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ እምነት የአንድ 'ፎክ' ወይም ቡድን ቁልፍ የመገለጫ ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን ረቂቅ የሆነ የእውቀት ደረጃ ነው፡፡ ስለዚህ ለምርምር (ለጥናት) ተግባር ጠቃሚ የሆኑ የፎክሎር ዓይነቶች በመሆናቸው ተጨባጭ ድርጊቶችንና ባህላዊ መገለጫዎችን መመልከት አለብን በማለት ያስረዳል (Mullen 2000፡ 120-122)፡፡

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ከሃይማኖታዊ ቀኖናዎች ውጭ በጋራ የሚያምኑባቸው፣ በዘልማድ በድርጊት የሚያከናውኑዋቸው፣ በትረካም የሚገልፁዋቸው 'ፎክ' ወይም ትውፊታዊ እምነቶች መካከል የሃይማኖት መቻቻልን ከሚያሳዩት መካከል 'ዋቃ' ፈጣሪ ሆኖ በዋቃ የሚያምኑትን ከዋቃ የሚያገናኙ አያንቱዎች ዋንኛው የትኩረት ነጥብ ናቸው።

### 4.2.1 ዋቃ (ፈጣሪ) እና አያንቱ (መልእክተኛ)

ዋቃ ፈጣሪ ማለት ነው፡፡ በማንኛውም የሥነ-ፍጥረት ሚት እንደሚተረከው ሁሉ ዋቃ ምድርንና ሰማይን፣ ኅያውንና ግዑዝ ፍጥረታትን የሠራ ሰማያዊ አምላክ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በሰው እና በፈጣሪ መካከል አገናኝ የሆነ ሰው ደግሞ አያንቱ ይባላል። በትውፊታዊ እምነቱ መሠረት ዋቃና አያንቱ አንዱ የፈጣሪ ሌላው የፍጥረት ግንኙነት አላቸው። አያንቱ የዋቃ ፍጡር ሲሆን ከሌሎቹ ሰዎች የተለየ ስጦታ ያለው፣ በዋቃ የተመረጠ፣ መንፈሱ ያረፈበት፣ ወዘተ፣ ነው ተብሎ የሚታመንበት ወንድ ወይም የሚታመንባት ሴት ነች[15]።

አያንቱ በዋቃና በአማንያን መካከል እንደ አማላጅ፣ እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል መንፈሳዊ መሪ (ritual leader) ነው። አያንቱ የዋቃ መልእክተኛ ሆኖ የሚያማልድ፣ እረኛ፣ ጠባቂ ተደርጎ ይታያል፡፡ አንድ አያንቱ ከሌላው አያንቱ የተለየ መንፈሳዊ ኀይል እንዳለው በእምነቱ ተከታዮች ይታመናል። አያንቱዎች በተሰጣቸው መንፈሳዊ ኀይል አንዱ ከሌላው ይለያያሉ። ለምሳሌ በአማንያኑ ዘንድ እንደሚታመነው ጉምን ወደ ውሀ የሚለውጥ አያንቱ አለ። ድርቅ በሆነበት ዘመን ወይም ዝናብ ከሚጠበቅበት ጊዜ ሲዘገይ ዝናብ ማዝነብ የሚችል አያንቱ አለ፡፡ የታመመን ከመድሀኒቱ የማገናኘት ኀይል ያለው አያንቱ አለ። በእምነቱ መሠረት አያንቱዎች ለማህበረሰቡ የተለያዩ ችግሮችን በዋቃ ፈቃድ የሚፈቱ የዋቃ መልእክተኞች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ወደ እነሱ ዘንድ የእስልምና ወይም የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነኝ የሚለው ይህን ሃይማኖቱን እንደያዘ ችግሩን ለመፍታት ወደ አያንቱ ይሄዳል፡፡ አያንቱም ቢሆን

[15] አያንቱ አለሙ ቱፋ፣ አያንቱ ሁሴን፣ አያንቱ ቦንቱ እና አያንቱ ሞቲ (የቡድን ውይይት ግንቦት 28/ 2009)

የእስልምናም ወይም የክርስትና (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ) ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። አያንቱዎች እንደ የክርስትና ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተቋም አባል ይሁኑ እንጂ ዋንኛ ስራቸው በዋቃ ደንብ የሚተዳደሩ ናቸው።

የአያንቱ መንፈስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መንፈስ ሲሆን መራቂው ከተመራቂው ጋር ተወራራሽ መንፈስ አለው። አንጋፋ የሆነ አያንቱ ከሚፈፅመው ሥርዓት መካከል ዋንኛው አዳዲሶችን አያንቱዎች መመረቅ፣ ግዴታዎችን ማሳወቅ እንዲሁም ማማከር ነው። ይህም ለምሳሌ፡- ይህን አታድርግ! ይህንን አድርግ! ለዚህ በሽታ እንደዚህ ዓይነት መድኃኒት ሥጥ፣ ወዘተ፣ የሚሉ መመሪያዎች ይገኙበታል። በዚህ ሁኔታ አንድ አያንቱ መጥፎ መንፈስን ምን ማድረግ እንዳለበት፤ በክፉ መንፈስ የተያዘ ሰው ሲመጣ እንዴት እንደሚፈታ፤ እንደሚታሰር፣ እንዴት ማውገዝ፣ እንዴት መመረቅ፣ ወዘተ፣ እንዳለበት ይማራል፡፡

አያንቱ መሆን ከዋቃ የሚሰጥ እንደሆነ ቢታመንም ከታወቁት የሃይማኖት ተቋማት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆንን አይከለክልም። አያንቱ ስለሆነም ከሃይማኖት ተቋሙ አባልነት አለመውጣቱ አንዱ ነው። ሌላው በተለያየ መልኩ በአያንቱ የዋቃ አማለጅነት የሚያምኑ ሰዎች ልክ እንደ አያንቱ የሁለቱ ሃይማኖት ተቋም አባል መሆናቸው እና ሁለቱንም እምነት አብረው ለእነሱ በገባቸው መንገድ አስማምተው ማመናቸው ነው። በአጠቃላይ ከአያንቱ ቤት ሙስሊም፣ ክርስቲያን አለመባሉ ነው። አያንቱ የሚከለከላቸውን ድርጊቶችና እንዲበላ የማይፈቀድለትን ምግብ የእስልምናም ሆነ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች እንዳይበሉ ጥንቃቄ ማድረጋቸው ሌላው የሃይማኖት መቻቻል መገለጫ ነው።

አያንቱ ለአማኞቹ አገልግሎት የሚሰጠው በራሱ ግቢ ውስጥ ለብቻ በተሰራ “ገልማ” (ቤት) ነው። ‘ገልማ’ ለዋቃ ምስጋና ማቅረቢያ ወይም የአምልኮት ማከናወኛ የጸሎት ቤት(‘shirine’) እንደማለት ነው። የገልማ ባህላዊ አገልግሎት የተቸገረ ወይም አንድ የባህላዊ እምነቱ አካል የሆነ ሥርዓት ለመፈጸም ለሚመጣ ሰው ማስተናገጃ በሳምንት በተወሰኑ ቀናት እንዲሁም በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ለዋቃ ምስጋናና መስዋእት ማቅረቢያ ቤት ነው።

የእስልምናም ሆነ የኢ.ኦ.ተ.ቤ አማኝ አያንቱዎች ገልማን በተለምዶ ‘መስጊድ’ በሚል ይጠሩታል። ወይም በገልማና በመስጊድ መካከል የተለያየ ትርጉም አይሰጡትም። ገልማዎች በተለይም በገጠር ከሚሰሩ ከማንኛውም መኖሪያ ቤቶች በቅርጽ የጎላ ልዩነት የላቸውም። ልዩነቱ በአማኙ አእምሮ ውስጥ ወይም በስተጀርባው ያለው የእምነትና የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት ማከናወኛ ትእምርትነት ነው፡፡

በአያንቱ የሚያምኑ ሰዎች የተለያየ ችግር ሲገጥማቸው ለምሳሌ ሲታመሙ ወይም የቅርብ ሰው ሲታመም፣ የተካካዱ ሰዎች ለመተማመን እና በሌሎችም ምክንያቶች ከተቸገሩት ችግር እንዲያወጣቸው ወይም መፍትሄ እንዲጠቁማቸው በአመቻቸው ወቅት ይሄዳሉ። ከዚህ ውጭ ህጻናት ሲወለዱ ለማስመረቅ እና አያንቱ ዋቃን የሚያመሰግንበት ቋሚ ቀን በአመት አንዴ አንዳንዴ ሁለቴ የታወቀና ቋሚ ቀን አለው። አንድ አያንቱ ለዋቃ ግብር የሚያቀርብበት ቋሚ ቀን ሊኖረው ግድ ሲሆን የአያንቱውን ለዋቃ ምስጋናና ግብር ማቅረቢያ እለት የሚወስነው

አያንቱነታቸውን መርቆ ያጸደቀው አንጋፋ መንፈሳዊ መሪ ነው። ይህ ቀን ከቅርብም ሆነ ከሩቅ መንገድ አቋርጠው ወደ አያንቱ ዘንድ በሚመጡ አማኞች ደምቆ ይከበራል። በዚህ ቀን አያንቱ ዘንድ መምጣት እንዲሁም ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ መቅመስ በረከት እንደማግኘት ይቆጠራል። አያንቱም በዚህ ቀን ማንንም መጥራት ወይም መጋበዝ አይጠበቅበትም አማኙ በራሱ ቢችል ምግብና መጠጥም ይዞ ባይችል ባዶ እጁን ታዳሚ መሆን ይችላል።

ለክብረ በአሉ ተብሎ የመጣ የእርድ ከብት እስከ በአሉ ማጠናቀቂያ ታርዶ (ለክርስቲያኑ ለብቻ ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዩ ለብቻ ይታረዳል) ማለቅ አለበት። ምግቡ ስጋ ከሆነ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለብቻ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ለብቻ ይበላሉ። የሚጠጣው ግን በጋራ ሲሆን አንዱ በጠጣበት የቡና ስኒ ሌላው እየጠጣ ይገባበዛል። በዚህን ቀን ቀደም ብለው ስዕለት ተስለው የተሳካላቸው እንደ ስእለታቸው አይነት ይዘው ይመጣሉ። ስዕለቱ የሚታረድ ከብት፣ የተዘጋጀ ምግብ የሚፈላ ቡና የሚጨስ እጣን ወይም ሰንደል እና መሰል ነገሮች ከሆኑ በዚሁ ዕለት አገልግሎት ላይ ይውላል። ለቀጣዩ አመት ክብረ በአልም የሚሳሉ ካሉ ሰው በተሰበሰበበት ወይም በአርምሞ የሚሳሉ የእምነቱ ተከታዮች ስዕለታቸውን ነግረው ወደየመጡበት ይመለሳሉ።

#### 4.2.2 ወሊዩ (አውልያ)

ወሊዩ በተሰጣቸው የተለየ መንፈስ ስለ አንድ ሰው ወይም ስለ አንድ ክስተት የወደፊት እጣ ፈንታ ይተነብያሉ። ትንቢቱም እውን ይሆናል። በሰው ሊፈጸሙ  የማይችሉ “ተአምር” የሚያስብሉ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ። ወለዩ የሚናገረውን ትንቢትም ሆነ ሌላ ምን መቼ ለማን? እንደተናገረ ያውቃል። የተጣላን ማስታረቅ፣ ከሰዎች የሚፈልገውን ጠይቆ የማያጣ። በማህበረሰቡ ዘንድ መልካም የሚባሉትን የሚያደርግ በተቃራኒው ካሉ እኩይ ተግባራት የራቀና ለሌላው መልካም አርአያ የሆነ፣ የሚቃወሙትን ከረገመ እርግማኑ መሬት ጠብ የማይል ሰው ነው። እነዚህን ከሌላው ሰው የሚለዩ ተግባራትን ለመፈጸም ያስቻለው በላው ላይ ያለው መንፈስ ነው። ይህም መንፈስ ዋቃ ለመረጣቸው ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነው።

አያንቱና ወሊዩ ተመሳስሎ አላቸው። ተመሳስሏቸውም የተለየ መንፈስ ከዋቃ የተሰጣቸው፣ እንደ ማንኛውም ሰው የተለያዩ ተግባራት ላይ የሚሰማሩ፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መንፈሳቸው አይወደውም በሚል ክልከላ ከሚጣልባቸው በስተቀር የሚሳተፉ፣ ሰዎች የሚያስቡትን ሳይናገሩ ማወቅ፤ ዋቃን ለምነው የማይከለከሉ። ለዋቃ የተለየ የምስጋና ቀን ያላቸው ናቸው። ወሊዩ ከሞተ በዚያው በገልማው አካባቢ ይቀበራል። በቀብር ቦታውም መንፈሳቸው እንደሚኖር ይታመናል። በመቃብር ስፍራው በየአመቱ ይመጣ የነበረም ሆነ አዲስ አማኝ ቀደም ሲል ይፈጽም የነበረውን ክዋኔ በሟቹ ወሊዩ ስም ይፈጽማል። ወደ  ወሊይ  የሚሄድ ማንኛውም ተጓዥ ለሚኖርበት አካባቢ፣ በተለይም ለቤተሰቦቹ “በረከት ይዞ ይመለሳል” ተብሎ ስለሚታመን በክብረ-በዓሉ ላይ ለመገኘት ሩቅ መንገድ ተጉዞ ይሄዳል። ወሊዩ የሚባሉት በአብዛኛው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ የሚከተሏቸው፣ የሚያከብሯቸውና በአመታዊ ክብረ በአሉ ላይ የሚሳተፉት ግን የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ. ሃይማኖትአማኞች ጭምር መሆናቸው ዋና የትኩረታችን ነጠብ ይሆናል ማለትነው።

ተከታዮቻቸው አውልያቸው (መንፈሳቸው) የጠየቁትን ይሰማል የሚል እምነት ስላላቸው የወልዩውን የቀብር ቦታ የአምልኮ ስፍራ አድርገው ይገለገሉበታል። በመሆኑም በዚሁ ስፍራ በመገኘት አውሊያው የሚፈልጉትን እንዲያደርግላቸው ይለምናሉ። ስዕለት ይሳላሉ። ወሊዩው በህይወት ሳሉ ያደርጉት የነበረውን አመታዊ ጉዞም አውሊያው ከሞቱ በሁዋላም አያቋርጡም። በዚሁ የመቃብር ስፍራ የተለያዩ እምነታዊ ክዋኔዎችን፣ ለምሳሌ፡- ሀመቺሳ እንዲሁም የአቴቴ ሥርዓተ-ክዋኔዎችም ይከውናሉ። ጭንት ሄጠሩና በሽምጊልና አልተማመን ያሉ ግለሰቦች ወደዚህ ስፍራ በመምጣት በመሀላ ይተማመናሉ። አንዳንድ ሰዎችም "አውልያቸው ጠርቶኛል" በሚል በመቃብር ሥፍራው ለረዥም ጊዜ ቀዬያቸውን ለቀው፣ ቤተሰቦቻቸውን ትተው በምናኔ ይኖራሉ።

በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የአውልያ ማምለኪያ ስፍራዎች ሶስት ናቸው። እነዚህም ኡጁባ አባ-ሴራ፣ ኡጁባ ሀጂ-ፈጂ እና ኡጅባ ሀጂ ናስር ሲሆኑ ኡጁባ ሀጂ ፈጂ እና ኡጅባ ሀጂ ናስር ለዚህ ጥናት በምልከታም ሆነ በቃለ-መጠይቅ መረጃ የተሰበሰበባቸው ቦታዎች ናቸው። ሁለቱም በዘመን የሚራራቁ ቢሆንም ተመሳሳይ ስጦታ የነበራቸውና ዛሬም የዘር ሀረጋቸው የቀብር ስፍራውን በበላይነት በመጠበቅ በዚያው አካባቢ ይኖራሉ። የሁለቱም የአምልኮ ሥፍራ መሥራቾችም ሆኑ አሁን የሚያስተዳድሩት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በእነዚህ ስፍራዎች የበቀሉ የተፈጥሮ ይሁኑ ይሆነኝ ተብለው የተተከሉ ዛፎች ስለማይቆረጡ ቦታው በደን የተሸፈነ ነው። በሁለቱም የአምልኮ ሥፍራዎች የሚሳተፉት የኦርቶዶክስ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን ልብ ማለት አስፈላጊ ይሆናል።

ሀጂ ፈጂ የቦታ ስም ነው። ወሊዩ የነበሩትና ከሞቱ በኋላ አውልያቸው የሚመለከውና የሚከበረው ሱከሬ አምቦ ተብሎ ይጠራል። "ሀጂ-ፈጂ" በኡጁባ ውስጥና ዙሪያ "የሚገኝን ዛፍ የቆረጠ ሰው ለተንኮልና ለጥፋት የሚመጣን አውሊያቸውን የሚጠብቁ ንቦች ያጠፉታል፤ ጉዳት ያደርሱበታል" የሚል ትርጉም አለው።"[16] ወሊዩ ሱከሬ አንቦ የኖሩበት ዘመን በትክክል አይታወቅም፤ ይሁንና ከሶስት ትውልድ በፊት ነው የሚሉ ይናገራሉ። በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ ካሉ የገጠር ከተሞች አንዷ በሆነችው መራሮ ከተማ አቅራቢያ በግምት በ5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። የአምልኮ ሥፍራው ተጠብቆ እንዲቆይና ወሊዩው በህይወት እያሉ ይደረግ የነበረው አመታዊ ክብረ በዓል ቀጣይነት እንዲኖረው ያደረጉት ልጆቻቸው ናቸው። አንዱ ሲሞት በሕይወት ያለው እየተተካ ይቀጥላል፡፡ ከእርሳቸው በፊት ቦታውን የጠበቁ አውልያውን ያከበሩ አባቶች መቃብርም በዚሁ ሥፍራ ይገኛል።

የባለ አውሊያውን ዘመዶች ጨምሮ ማንኛውም ሰው መቀበር ስለፈለገ ብቻ ሊቀበር አይችልም። የሚፈቀደው ለባለ አውሊያው የመጀመሪያ ወንድ ልጅ እንዲሁም ለእርሱ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ እያለ ስድስት ሰው ተቀብሮበታል። ከዚህ በኋላ የሚቀበሩት የመጨረሻው አንድ የልጅ ልጅ ብቻ ቀርተዋል። በሀውልቶቹ ዙሪያ ትልልቅ የአበሻ ጥድ ዛፎች ይገኛሉ። ዛፎቹ ረዘም ያለ እድሜ እንዳስቆጠሩ አይቶ ለመገመት ይቻላል። በደርግ ዘመን ለሰፈራ ተብሎ በአካባቢው የነበሩ ዛፎች

[16] ሀጂ ኢብራሂም፣ እድሜ 47፣ (ቃለ-መጠይቅ ታሀሳስ16 ቀን፣ 2008)።

ሲመነጠሩ በኡጁባ ሀጂ ፈጂ ዙሪያ ያሉ ዛፎች እንዳልተቆረጡ ይናገራሉ።[17]

ወደ ኡጁባ ሀጂ ፈጂ ማንም ሰው ያለ ጉዳይ አይገባም። ከብትም እንዳይገባ የአካባቢው ሰው ይጠነቀቃል። ዛፎቹ የተከበሩ ናቸው፡፡ አንድ ንፋስ የጣለው ትልቅ ዛፍ ነበር፡፡ በአገልግሎት ላይ ስላልዋለበት ምክንያት ጥያቄ አቅርቤ አቶ ተሾመ ሲመልሱ፡- "ይህ የተቀደሰ ቦታ ነው፡፡ ምንም ነገር አይነካም፡፡ ከተነካ ግን ይፈጅናል! ብለን ስለምናምን ማንም ሰው ዛፍ አይነካም። ወደ ስፍራው ያለ ምክንያት መግባት አይቻልም፡፡ ከገቡም በኋላ መዋሸት፣ ክፉ ነገር መናገር አይገባም" [18] የሚል ነበር፡፡

የአምልኮ ሥፍራው ለዕርቀ-ሰላም ማከናወኛም ያገለግላል፡፡ ለዚህ ተግባርም ሰዎች ራቅ ካለ ቦታ ጭምር ይመጣሉ። አንድ ሰው ከሩቅ አካባቢ መጥቶ "እንዲህ ተበድያለሁ" ብሎ ለኡጁባው የበላይ ጠባቂ ይናገራል። ይህም 'በዳይ ነው' የተባለውን ሰው ጥፋተኛ መሆን አለመሆኑን ሌሎች ሽማግሌዎችን ጨምሮ እንዲያረጋግጡ ያደርጋል። "በዳይ ነው" የተባለው ሰው የመኖሪያ አካባቢው ሩቅ ከሆነ፤ በአምልኮ ስፍራው አካባቢ የሚኖሩ ሽማግሌዎች "በዳይ ነው" ወደ ተባለው ሰው መልእክት ይልካሉ።

በዳይና ተበዳይ በቀጠሯቸው መሠረት በአምልኮ ሥፍራው ተገናኝተው በመሀላ ይተማመናሉ። ኡጁባ ሀጂ ፈጂ የመጣ ሰው አይዋሽም ተብሎ ስለሚታመን ዕርቁ የፀና ይሆናል። በአምልኮ ሥፍራው በዓመት አንድ ጊዜ ከሳምንት በላይ የሚቆይ ክብረ-በዓል ይከወናል። የዚህ በዓል ታዳሚዎችም ከተለያዩ ስፍራዎች ለምሳሌ ከአጎራባች ዞንና ክልል ጭምር የሚመጡ የኢ.ኦ.ተ. እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይገኙበታል። ሲመጡም የተለያዩ የማምለኪያ ዕቃዎችን ይዘው ነው። ከእነዚህ ዕቃዎች መካከል ለምሳሌ ደንቄ፣ ከበላ፣ ዲቤና ሌሎች እንዲሁም ባህላዊ ልብሶች በተለይም ጊሼ የሚባለውን ልብስ ለብሰው ስዕለት ያለበት ስዕለቱን ይዞ ይመጣል።[19]

በኡጁባ ሀጂ ፈጂ ሌላው የሚደረገው የረመዳን ጾም ሊጀመር ሳምንት ሲቀረው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ሰንጋ አርደው ፆም ይይዛሉ። እንደሚታመነው አውልያው በጣም የሚታወቅበት የተደበቀን እውነት በማውጣት ነው። እዚህ ቦታ የተጣሉ ሰዎች መጥተው "ሀሰት አይናገሩም" መጥተው ከዋሹ "ይፈጀናል" ስለሚሉ አይክዱም። ያጠፋም ማጥፋቱን ያላጠፋም ንፅህናውን፤ ያለ ምስክር ከሳሽና ተከሳሽ ይተማመናሉ።[20] በአጠቃላይ እምነቱም ሆነ ክዋኔው ይህን ሲመስል ከእስልምናም ሆነ ከኢ.ኦ.ተ. ሃይማኖት ተከታዮች ለኡጁባ ሀጂ ፈጂ ትልቅ የጋራ የሆነ ከበሬታ አላቸው።

ኡጁባ ሀጂ ናስር[21] የሚባለው ደግሞ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ከሚገኙ የገጠር ከተሞች መካከል

---

[17]አብዱል ቃድር ሱከሬ፣ እድሜ 58፣ (ቃለ-መጠይቅ ታህሳስ 16 ቀን፣ 2008)።
[18] አቶ ተሾመ ገለቱ፣ እድሜ 46፣ (ቃለ-መጠይቅ ታህሳስ 17/2008)።
[19] አብዱል ቃድር ሱከሬ፣ እድሜ 58፣ (ቃለ-መጠይቅ ታህሳስ 16 ቀን፣ 2008)።
[20] አብዱል ቃድር ሱከሬ፣ እድሜ 58፣ 8 (ቃለ-መጠይቅ ታህሳስ 16 ቀን፣ 2008)።
[21]በአርሲ ክፍለ-ሀገር ውስጥ ከግራኝ ወረራ በፊት፣ ከባሌ ድንበር (ከዋቤ ወንዝ) ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ቤተ-ክርስቲያንና ገዳማት መኖራቸውን ኋላ ላይ ደግሞ በወረራው ምክንያት ከአካባቢው መውደማቸው

አንዱ በሆነው ሲርቦ ከተማ አቅራቢያ ሁለት ኪ.ሜ ገደማ ይርቃል። የሀጂ ናስር መኖሪያ የነበረውና አሁን የመቃብር ስፍራቸው የሆነው ቦታ መጠሪያ ሄርሻ፣ ቁባ፣ ገሞ[22] በመባል በሶስቱም መጠሪያ ይታወቃል። ወሊዪ የነበሩት ሀጂ ናስር በዚህ ቦታ ለአምልኮ፣ ለምስጋናና ለስዕለት የሚመጡት በቦታው ላይ የሀጂ ናስር መቃብር ስላለ አውሊያቸው የሀሳባችንን ይሞላልናል በሚል እምነት ነው። “እኔ የዚህ ቦታ ጠባቂ አይደለሁም። ቦታውን የሚጠብቀው የሀጂ ናስር አውልያ ነው” የሚሉት ስለ ቦታው መረጃ የሚሰጡት እንዲሁም ስዕለት የሚቀበሉና በአጠቃላይ እዚያ ቦታ ለሚደረገው ማንኛውም ጉዳይ ተጠሪ የሆኑት ከሀጂ ናስር ጋር የሚገናኙበትን የትውልድ ሀረግ ከራሳቸው ስም ጀምረው ሲቆጥሩ የባለ አውልያው አስረሀንደኛ ልጅ ይሆናሉ።[23]

በአጠቃላይ ባህላዊ እምነቶችና ሥርዓተ-ክዋኔዎች በኢ.ኦ.ተ እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚካሄዱ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ እነዚህም በአብሮ መኖር ሂደት ውስጥ የገነቡትን የመቻቻል እሴቶች የሚያሳዩ ክዋኔዎች ናቸው። ከዚህ ውጭ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ባህላዊ እምነቶቹን እን ኋላቀር ልማድ ይመለከታሉ። በመሆኑም አማኞቹ በግልፅ ሲያከናውኑዋቸው አይታዩም፡፡ ባህላዊ እምነቶችን ከዋናው ሃይማኖታቸው ጎን ለጎን የሚያከናውኑት የእስልምና እና የኢ.ኦ.ተ. ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በሁሉም የአምልኮ ሥፍራዎች የሚሳተፉት የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን ልብ ማለት አስፈላጊ ይሆናል።

የአያንቱ አምልኮ እንደ ማንኛውም እምነት በለውጥ ሂደት ውስጥ ይገኛል፡፡ ለውጡ ሁለት መልኮች አሉት። አንደኛው ለውጥ የክርስትናውም ሆነ የእስልምናው አስተምህሮ እየጠነከረ መሄድ። የሁለቱ ሃይማኖት መምህራን በየመድረኩ “ባእድ አምልኮ ነው” በሚል አማኞቹ ትክክል እንዳልሆኑ መስበካቸው ዋንኛው ምክንያት ነው። በዚህም ምክንያት በተለይ ወጣቶቹ ቤተሰቦቻቸውን በመቃወም “የአያንቱ መንፈስ ትክክል አይደለም” በማለት እምነቱን እያጣጣሉ፤ ጠንከር ሲልም ገልማዎቻቸው ድረስ በመሄድ የረበሹበት አጋጣሚ እንደነበር ከአያንቱዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል። ሌላው ለውጥ አያንቱዎች ተሰባስበው ከተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ለመከላከል እና እንደ አንድ የእምነት ተቋም እውቅና ጠይቀው ያገኙበት ነው። ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በመንግሥት እውቅና ተሰጥቶት “የአያንቱ መላከ ውቃቢ[24] እምነት” ተብሎ እንደ አዲስ እምነት ተቋቁሟል። “የአያንቱ መላከ ውቃቢ እምነት” ልዩ ገጽታው

…በዚሁ በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ውስጥ ሄርሻ ቀበሌ ሲርቦ ከተባለች ከተማ በታች የማርያም ጽላት ነበረች። በዚያ ቦታ ሀጂ ናስር የሚባል እዚያች ቦታ አርፏል። ያኔ በግራኝ ጊዜ ክርስቲያኖች ሲሰደዱ ሀጂ ናስር ያቺን ቦታ አረፈባት። በዚህ ምክንያት…በግንቦት ወር አካባቢ ያንን በዓል ያከብራሉ። አሁንም በየአመቱ እያከበሩ ነው (ወርቁ፤ 2000፡35)።

[22] ሄርሻ በአቅራቢያው ያለው ወንዝ ሥም ሲሆን አካባቢው በሙሉ በዚሁ ሥም ይጠራል። ቁባ ማለት እንደ ማንኛውም ሰው መቃብር እንዳልሆነና መቃብሩ ላይ ሀይል እንዳለና ከፍ ያለ እንደሆነ ለመግለጽ ሲባል ቁባ ይባላል። ገሞ በዚያ ዙሪያ ያሉ ዛፎች በየትኛውም አካባቢ ካለ የዛፍ ዝርያ ቢመሳሰልም አውሊያ ያለበት የበቀለ በመሆኑ ወሊዪው መንፈሳቸው አድሮበታል ተበሎ ስለሚታመን ገሞ ይባላል።

[23]መሀመድ፣ ሀጂ አሊይ፣ ከቢል ሀጂ፣ ሄርሾ፣ ጃራ፣ ውልሌ፣ ጊኖ፣ አበይ፣ ተማም፣ ሙደር፣ ሀጂ ናስር በማለት ነው (ቃለመጠይቅ፣ ታህሳስ 14/ 2008)።

[24] “መላከ” የሚለው ቃል እንዲለወጥ የተለያዩ አካላት ስለጠየቁ ቃሉ በሌላ እንደሚተካ ወይም እንደሚቀር ጠቁመዋል።

የእምነቱ መስራች አባላት የኢ.ኦ.ተ.ቤ እና የሙስሊም ሃይማኖት ተከታይነታቸውን ሳይተው የዚህ እምነት መስራችና ባለቤት መሆናቸው ነው።

## 5. ማጠቃለያና ይሁንታ

ጥናቱ ከጅምሩ ይዞት የተነሳው ዐቢይ ዓላማ በአርሲ ዞን በተለይም በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ለረዥም ዘመናት አብሮ በመኖር ሂደት ገቢራዊ የሕይወት ገጽታ የተፈጠረውንና ሥርፀት አግኝቶ የነበረው፣ የመቻቻል ባሕርያትንና የመገለጫ ዓይነቶች ከሆኑት መካከል በመጥፋት ስጋት ውስጥ ያሉትን ጡት መጣባትና ባህላዊ እምነትን የሚመለከቱ ናቸው። ይህንንም ለሌሎች እንዲያውቁት በጥናት ላይ ተመስርቶ በመጻፉ ማስተዋወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ጥናቱ ተከናውኗል። እነዚህ ሁለት ርእሰ ጉዳዮች በዚህ ጥናት ሙሉ በሙሉ ተጠንተዋል ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም አላማው ማስተዋወቅና በቀጣይ ሌሎች አጥኚዎች በጥልቀት እንዲጠኑት መነሻ ጥናት እንዲሆን የተጠና ነው። ከዚህም ባለፈ ለሰላማዊ አብሮነት አስተዋጽዎ ያላቸውን የሃይማኖት መቻቻል ለማስተዋወቅ ይህ ጥናት ጠቃሚ ግብአት ነው።

በአጠቃላይ በተይም በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰቦች መካከል ለረዥም ጊዜ አብሮ በመኖር ሂደት የተፈጠሩና ሥርፀት ያገኙ ፎክሎራዊ የመቻቻል ባሕርያት ምግባራዊ እሴቶች ምን እንደሚመስሉ፣ ምን ማህበራዊ ተግባር እንደሚያሙዋሉና እንዴት እንደሚገለፁ ተመልክተናል፡፡ ምግባራዊ እሴቶቹ በአንድ በኩል ከገሀዱ ዓለም ሕይወት ወይም የአኑዋኑዋር ስልትና ፍልስፍና የመነጩና የተቃኙ ሆነው እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቦቹ መካከል ያሉትን የሃይማኖት ልዩነቶች በመቻቻል የሚመሩ፣ በባህል የተደነገጉና የተቁዋቁዋሙ ለዘላቂ ሰላም መሠረትና ዋስትና ተግባራዊ ሕጎች ሆነው ይሠራሉ፡፡ እንደተመለከትነው እሴቶች ወይም የመቻቻል ባሕርያቱ በተለይም በእስልምናና በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል 'መቻቻል' የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ፣ መርህና ተግብራዊ ድርጊቶች በአጠቃላይም እውነተኛ ትርጉም የሚያካትቱ ገጽታዎችን፣ ማለትም፡- አንዱ የሌላውን ጎልውና ተቀብሎ እውቅና መስጠትን፣ መከባባርን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮነትን፣ አንድነትንና ሰላምን፣ ወዘተ፣ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በአንፃሩ ሲታይ እነዚህ በእስልምና እና በኢ.ኦ.ተ.ቤ አማንያን መካከል ሥር የሰደዱ የመቻቻል መገለጫ ባሕርያት በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ ዘንድ ሥርፀት አግኝተዋል ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም።

ጡት መጥባትም ሆነ ባህላዊ እምነት በመጥፋት አደጋ ላይ ናቸው። በተለይም ባህላዊ ዝምድናን በመመስረት ሂደት ክዋኔውን ለመመልከት አጥኚዋ ያደረገችው ሙከራ አልተሳካም። ምክንያቱ ደግሞ ባህላዊ ክዋኔው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየቀረ መሆኑ ነው። ባህላዊ እምነት በተለይ ወጣቱ እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋማት በእምነቱ ተከታዮች ላይ የሚያደርጉት ተጽእኖ እንዳይቀጥል ከሚያደርጉት ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው።

በሃይማኖታዊ አውድ ውስጥ መቻቻልን ለመረዳት ስንሞክር በመጀመሪያ በአእምሮአችን የሚፈጠረው ለጎልውና አስፈላጊ በሆነ በባህል ተቀባይነት ባለው ደንብ ላይ የተመሠረተ የአለመቀበል (rejection) ዋነኛ ጥያቄ የሆናል፡፡ እንዲህ ያለው አለመቀበል ለሁሉም የቻይነት (tolerant) ባሕርያት ዓይነቶች

አስፈላጊ ሁኔታ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚያም፣ "የሌሎችን ሰዎች እምነት በሚመለከት በዘወትራዊ ሕይወት መቻቻልን በገቢር የምንተረጉመው ተቀባይነት ባላቸው ተገቢ ምክንያቶች የማንቀበለው ነገር መኖሩንም ጨምረን ከገለፅን ነው፡፡ የሌሎችን ሀሳቦች፣ እምነቶች፣ አመለካከቶች፣ ድርጊቶች ጨርሶ የማንቀበል ከሆነ እንዲሁም 'ሌላነት' ('otherness') የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ ያለውን እሴት (ጥቅም) የማናደንቅ ከሆነ 'ቻይነት' አያስፈልገንም" (Habermas 2004፡ 10) በማለት ያጠቃለለው ሀሳብ፣ በአንድ በኩል በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች የሚታዩትን ልዩነቶች በሌላ በኩል ደግሞ በእስልምና እና *በኢ.ኦ.ተ.ቤ* መካከል የዳበሩትን የመቻቻል ባሕርያት ደረጃና ሥርፀት የሚገልፅ ይሆናል፡፡

**ይሁንታ**

አጥኚዋ የጥናቱን ውጤት መነሻ በማድረግ በቀጣይ ቢደረግ የምትለው።

1. የሃይማኖት መቻቻልን የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶች ተለይተው በመንግስታዊ አካል እውቅና ቢሰጣቸው፣

2.ባህላዊ የእምነት ስፍራ የሆኑት ቦታዎች ጥበቃ ቢደረግላቸው፣

3. በመጥፋት አደጋ ላይ የሆኑ በዚህ ጥናት የተነሱት እና ሌሎችም መሰል የመቻቻል መገለጫ እሴቶች ተጠንተው ቢለዩና ቢመዘገቡ።

## ዋቢ ጽሁፎች

የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ አስተዳደር። 2002። አጠቃላይ መረጃ። (ያልታተመ)።

ደስታ ተክለ ወልድ። 1962። *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት።* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

Abbink, Jhon. 1998. *A Historical-anthropological approach to Islam in Ethiopia*: Issues of identity and politics; Journal of African cultural studies, Volume11, Leiden.

Abdullah, T. 2012. *"Co-existence and Harmony in a pluralistic world: Gulen movement as wording model,"* a paper presented at a conference on establishing and sustaining the culture of co-existence and mutual understanding organized by ministry of Federal Affairs.

Braukamper, Ulrich. 1992; *Religious Syncretism in Southern Ethiopia, Journal of* religion in Africa, Vol. 22, No. 3, pp. 194-207.

Federal Democratic Republic of Ethiopia, 2009; Central Statistical Agency; *2007 Population and Housing Census of Ethiopia*; Addis Ababa.

Motz, Marilyn. 1998. *The Practice of Belief*, Journal of American Folklore 111:339-355.

Fetterman, D.M. 2009. *Ethnography: Step-by-Step* (3rded), New Deli, Saga publication, Inc.

Habermas, JÜrgen.2004. "Tolerance: The Pacemaker for Cultural Rights", *Journal of Philosophy*, vol. 79, No 30.

Mullen, B. 2000. *Belief and the American Folk*. *Journal of* American Folklore, 113(448):119-143.

Murphy, Andrew. 1997. "Toleration, and Liberal Tradition," *Journal of Polity*, vol. 29, No. 4, pp. 593-623.

Newman, Jay. 1978. "The Idea of Religious Tolerance". *Journal of American Philosophical Quarterly*, Vol. 15, No. 3, pp 87- 195.

UNESCO. 1995. *Declaration of principles on Tolerance* proclaimed and signed by the Member States of UNESCO on 16 November 1995, Paris: UNESCO.